# የሞንትጎመሪ ኬርስ ክሊኒኮች
**(MONTGOMERY CARES CLINICS)**

**ካሳ ሩበን (Casa Ruben)**
የቀጠሮ ማስያዣ የስልክ ቁጥር (301) 445-2500

**ሲሲአይ (CCI) የጤና አገልግሎቶች Inc.**
ጌትዝበርግ ፣ሲልቨር ስፕሪንግ፣ታኮማ ፓርክ፣
የቀጠሮ ማስያዣ የስልክ ቁጥር፡- 1 (866) 877-7258

**ሲሲኤሲሲ (CCACC) የፓን ኤዥያ በጎ ፈቃደኞች የጤና ክሊኒክ**
ጌትዝበርግ፡- (240) 393-5950

**የሮክቪል ማህበረሰብ ሚኒስትሪስ(Community Ministries of Rockville)፡- ማንፊልድ ካሴማን (Mansfield Kaseman) የጤና ክሊኒክ**
ራክቪል፡- (301) 917-6800

**የሆሊ ክሮስ (Holy Cross) ጤና ጣቢያዎች**
አስፐን ሂል፡- (301) 557-1940
ጌትዝበርግ፡- (301) 557-1940
ሲልቨር ስፕሪንግ፡- (301) 557-1940

**የሜሪላንድ ኢስላሚክ ማእከል**
ጌትዝበርግ፡- (240) 912-4976

**የሜሪ ሴንተር የእናቶች እና የህጻናት እንክብካቤ**
ሲልቨር ስፕሪንግ፡- (844) 796-2797

**ሜርሲ (Mercy) የጤና ክሊኒክ**
ጌትዝበርግ፡- (240) 773-0300

**ሞባይል ሜዲካል ኬር (በርካታ ቦታዎች)**
የቀጠሮ ማስያዣ ስልክ ቁጥር፡- (301) 493-2400

**የሙስሊም ማህበረሰብ ማእከል የህክምና ክሊኒክ**
ሲልቨር ስፕሪንግ፡- (301) 384-2166

**ፕሮየክቶ ሳሉድ (Proyecto Salud)**
ዊትን፡- (301) 962-6173
ኦልኒ፡- (301) 260-1073

ለተጨማሪ መረጃ ይደውሉ 311 ወይም
(240) 777-0311

## የፕሮግራም ብቁነት የማረጋገጫ እና የድጋፍ አገልግሎቶች ቢሮ (OESS)

ለኬር ፎር ኪድስ (**Care For Kids**) ለማመልከት በሞንትጎመሪ ካዉንቲ የፕሮግራም ብቁነት የማረጋገጫ እና የድጋፍ አገልግሎቶች ቢሮ (OESS) በኩል ማመልከቻ መሞላት አለበት።

12900 Middlebrook Road, 2 ኛ ፎቅ
Germantown, MD 20874
(240) 777-3591

1401 Rockville Pike,፣ 1 ኛ ፎቅ
Rockville, MD 20852
(240) 777-3120

8630 Fenton Street ፣ 10ኛ ፎቅ
Silver Spring, MD 20910
(240) 777-3066

## የስራ ሰዓት፡-


ከሰኞ እስከ አርብ
ከ 8:30 ኤኤም እስከ 4:30 ፒኤም

ማምጣት ያለብዎት ሰነዶች፡-

◊ የገቢ ማስረጃ (ፔይስታብ፣ የታክስ ሪተርን፣ ወዘተ.
◊ የማንነት ማረጋገጫ (መንጃ ፈቃድ፣ የሥራ ፈቃድ መታወቂያ ( employment id)፣ ወዘተ.)
◊ የሞንትጎመሪ ካዉንቲ ነዋሪነት ማረጋገጫ (የቤት ኪራይ ውል፣ የፍጆታ /ዩቲሊቲ የክፍያ ደረሰኝ፣ ወዘተ.)
◊ ሌላ ማምጣት ያለብዎት ዶክመንት ካለ ለማወቅ አስቀድመው ይደውሉ።


ለተጨማሪ መረጃ ይደውሉ 311 ወይም
(240) 777-0311

## የጤና እንክብካቤ ይፈልጋሉ?
## የጤና ኢንሹራንስ የለዎትም?
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ቢሮ ሊያግዝዎ ይችላል።




## ሞንትጎመሪ ኬርስ
(MONTGOMERY CARES)

የጤና ኢንሹራንስ ለሌላቸው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ግለሰቦች (ዕድሜያቸው 18+) ።



## ኬር ፎር ኪድስ
(CARE FOR KIDS)
የሞንጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ዝቅ ተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰብ ስር ለሚኖሩ
እና የጤና ኢንሹራንስ ለሌላቸ ው ልጆች።



## የሞንትጎመሪ ለእርጉዝ እና አዲስ የወለዱ እናቶች ፕሮግራም
(MONTGOMERY PERINATAL PROGRAM)፡-
በሞንትጎመሪ ካውንቲ ለሚኖሩ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው እና ኢንሹራንስ ለሌላቸው ነፍሰ ጡር ሴቶች የቤት ውስጥ የጉብኝት አገልግሎቶች።

ለተጨማሪ መረጃ ይደውሉ 311 ወይም
(240) 777-0311

## ሞንትጎመሪ ኬርስ
(MONTGOMERY CARES)

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ክሊኒኮች ጥምረት ሲሆን፣ ዕድሜያቸው አስራ ስምንት ዓመት እና ከእዛ በላይ የሆነ እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው፣ ኢንሹራንስ ለሌላቸው የካውንቲ ነዋሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ እና የስፔሻሊቲ (primary and specialty) የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ይሰጣል።

**አገልግሎቶች ፣**

◊ የሕክምና አጠቃላይ ምርመራዎች

◊ መድሃኒት

◊ የላብራቶሪ ምርመራዎች

◊ የካንሰር ምርመራዎች

◊ ከስፔሻሊስቶች አገልግሎት ማግኘት መቻል

**የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ ለፕሮግራሙ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡-**

◊ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ከሆኑ

◊ ዕድሜዎ 18 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ

◊ ምንም አይነት የጤና ኢንሹራንስ ከሌለዎት (ይህም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡- ኳሊፋይድ የጤና ፕላን (Qualified Health Plan)፣ እንደ ሜዲኬድ ወይም ሜዲኬር ያሉ የስቴት ወይም የፌዴራል ኢንሹራንስ ፕሮግራሞች)

◊ ገቢዎ ከፌዴራል የድህነት ወለል 250% ወይም ከዚያ በታች ከሆነ

### ለማመልከት ፡-

ቀጠሮ ለመያዝ ለእርስዎ ቅርብ ወደሆነው **የሞንትጎመሪ ኬርስ (Montgomery Cares)** ክሊኒክ ይደውሉ። ምን አይነት መረጃ እና ሰነድ ይዘው መምጣት እንዳለብዎት ክሊኒኩን ይጠይቁ።

## ኬር ፎር ኪድስ
(CARE FOR KIDS)

በሞንትጎመሪ ካዉንቲ ውስጥ ላሉ እና በሌላ ስቴት ወይም ፌደራል ኢንሹራንስ ፕሮግራሞች ውስጥ ላልተመዘገቡ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች ልጆች ተመጣጣኝ የመጀመሪያ እና የስፔሻሊቲ (primary and specialty care) የጤና አገልግሎት ይሰጣል።

**አገልግሎቶች፡**

◊ የህጻናት ጤና ምርመራዎች (Well-child visits)
◊ የሕክምና አጠቃላይ ምርመራዎች
◊ የጥርስ ህክምና
◊ የአይን ህክምና
◊ መድሃኒት
◊ ከስፔሻሊስቶች አገልግሎት ማግኘት መቻል
◊ እና ሌሎችም...

**ልጅዎ የሚከተሉትን የሚያሟላ/የምታሟላ ከሆነ ለፕሮግራሙ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡**

◊ ዕድሜያቸው ከ 18 በታች ከሆነ
◊ በሜሪላንድ የህፃናት የጤና ኢንሹራንስ ፕሮግራምን ጨምሮ በማንኛውም የስቴት ወይም የፌዴራል ኢንሹራንስ ፕሮግራሞች ውስጥ ያልተመዘገቡ ከሆነ
◊ ቤተሰብዎ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሚኖር ከሆነ
◊ የቤተሰብዎ ገቢ ከፌዴራል የድህነት ወለል 250% ወይም ከዚያ በታች ከሆነ

### ለኬር ፎር ኪድስ

(CARE FOR KIDS) ፕሮግራም ለማመልከት፡- የፕሮግራም ብቁነት የማረጋገጫ እና የድጋፍ አገልግሎቶች ቢሮን (OESS) ያነጋግሩ።

## የሞንትጎመሪ ለእርጉዝ እና አዲስ የወለዱ እናቶች ፕሮግራምን በተመለከተ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ለሚኖሩ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነፍሰ ጡር ሴቶች ሁሉ የቤት ውስጥ ጉብኝት አገልግሎቶችን ይሰጣል። ፕሮግራሙ ኢንሹራንስ ሌላቸው ነፍሰ ጡር ሴቶች ድጋፍ ያደርጋል።

ሁሉም የፕሮግራም ተሳታፊዎች የነርስ ወይም የማህበረሰብ ጤና ሰራተኛ የቤት ውስጥ ጉብኝት እና የጉዳይ አስተዳደ ሮች (case managment) አገልግሎቶችን ያገኛሉ፣ ይህም የሚከተሉትን እና ሌሎች ተጨማሪ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡-

◊ ሪፈራል (Referrals)
◊ ከጤና እንክብካቤ አገልግልቶች ጋር ማገናኘት
◊ ድጋፍ፣ ትምህርት
◊ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ እርግዝና፣ ልጅ መውለድ፣ ከወሊድ በኋላ እና አዲስ የተወለደ ህጻን እንክብካቤን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ አገልግሎቶች እና መረጃዎች

የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ ለፕሮግራሙ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡-

◊ ነፍሰ ጡር ከሆኑ
◊ ዝቅተኛ ገቢ ወይም በፌዴራል የድህነት ወለል መሰረት 250% ወይም ከዚያ በታች ከሆኑ
◊ የሞንትጎመሪ ካዉንቲ ነዋሪ ከሆኑ

### እንዴት ማመልከት ይቻላል፡-

**የሞንትጎመሪ ለእርጉዝ እና አዲስ የወለዱ እናቶች የቤት ጉብኝት ፕሮግራም፡-** በ 240-777-4648 ወይም 240-777-3054 ይደውሉ

**ለሜዲኬድ (Medicaid) ለመመዝገብ እገዛ ከፈለጉ፡-ይህን ድረገጽ ይመልከቱ፣**

www.MarylandHealthConnection.gov ወይም ወደ ሞንትጎመሪ ካዉንቲ በ 240-777-1815 ይደውሉ